ሰኔ 8 ቀን 1990 ዓም

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት የአጽም በክብር ማሣረፍ ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀረበውን ሁለተኛ ሪፖርት በማሻሻል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያጸደቀው የቀብር ሥነስርዓት መነሻ ፕሮግራም

1. የቀብሩ ሥነስርዓት ከሚፈጸምበት በተቻለ መጠን ከስድስት ወር በፊት ዝርዝር ፕሮግራሙን ለመንግሥት በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ ነው።

2. የቀብሩ ሥነስርዐት ከሚፈጸምበት ዕለት በፊት በሚገኙት ስልሣ ቀናት ጀምሮ እንደአስፈላጊነቱ በተደጋጋሚ ስለቀብሩ ሥነስርዓትና ከፕሮግራሙ ውስጥ ለሕዝቡ መረጃ የሚሆኑትን ጉዳዮች ሁሉ በማብራራት በራድዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣዎች ገለጻ ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸም የማስታወቂያ አገልግሎት የሚገኘው ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም መሆኑን በመገንዘብ ባጀት ሊመደብለት ይገባል። የሥነስርዓቱ ፕሮግራም በተግባር እንዲውል ፈቃድ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ በውጭ አገር የሚገኙ የግርማዊነታቸው ወዳጆች ሁሉ ስለፕሮግራሙ ግንዛቤ እንዲያገኙ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል።

በበዓሉ ለመሳተፍ ለሚመጡት የውጭ አገር የክብር እንግዶችና በአገር ውስጥ ለሚገኙት የዲፕሎማቲክ አባላት የሚላከው ጥሪ በመሠረቱ በመስቀል አደባባይ በሚደረገው ሥነስርዓት እንዲካፈሉ የሚጋብዝ ሲሆን ፈቃደኛ የሆኑት ደግሞ በባዕታ ገዳምና በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሚደረገውም ሥነስርዓት መካፈል የሚችሉ መሆናቸውን የሚገልጽ ይሆናል።

የውጭ አገር የክብር እንግዶችንና የዲፕሎማቲክ አባላትን መስተናግዶ በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፕሮቶኮል መምሪያ ትብብር ይጠበቃል።

3. በዕለቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት ሁሉ ጸሎተ ፍትሐት ሌሊቱን ከሟቱ አሥራ ሁለት ሰዓት በፊት ይከናወናል። ልክ በሟቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቤተክርስቲያናት ሁሉ ደወላቸውን ያሰማሉ።

በቤተክርስቲያናት አካባቢ የሚፈጸሙ ሥነስርዓቶችን በሚመለከት ከጠቅላይ ቤተክሕነት ጋር በመመካከር ዝርዝር ፕሮግራም ወደፊት ይዘጋጃል።

ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውጭ ያሉ ቤተክርስቲያናት የራሳቸውን ፕሮግራም በማዘጋጀት በራሳቸው ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት በመታሰቢያ ድርጅቱ አማካይነት ለሕዝቡ ገለጻ በማድረግ የጸሎት ስርዓታቸውን ይፈጽማሉ።

የእስልምና ተከታዮች በየመስጊዶች ስለሚያደርጉት የጸሎት ሥነስርዓት ፕሮግራም ከእስልምና ሃይማኖት መሪዎች ጋር መታሰቢያ ድርጅቱ በሚያካሂደው ውይይት መሠረት ወደፊት ይወሰናል።

4. ከሚቴ በአሥራ ሁለት ሰዓት ንጉሣዊ ቤተሰቦች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገሮች የክብር እንግዶች በታዕካ ነገሥት የባዕታ ለማርያም ገዳም በመገኘት የግርማዊነታቸው አጽም በክብር በአደራ ከተቀመጠበት ቦታ ተነስቶ ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለመዛወር ጉዞ ሲጀምር በሚደረገው የመሸኛ ጸሎትና ሥነስርዓት ይሳተፋሉ።

5. የግርማዊነታቸው አጽም በተዘጋጀለት የክብር ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ከባዕታ ለማርያም ገዳም ተነስቶ በቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ፊትለፊት በንጉሣዊ ቤተሰቦችና በክብር እንግዶች ታጅቦ እስከ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ኀዳና አናት ድረስ ይሸኛል። ከባዕታ እስከ ድግማዊ ዐፄ ምኒልክ ኀዳና አናት ባለው መንገድ ግራና ቀኝ በቤተመንግሥቱ አካባቢ የሚገኙት የሶስቱ አብያተ ቤተክርስቲያናት ካህናትና መዘምራን በቅላይ ቤት ክህነት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሃዘን መግለጫ በመልበስ የአስከሬኑ አሸኛኘት ተካፋይ ይሆናሉ።

6. ንጉሣዊ ቤተሰቦችና የክብር እንግዶች ወደታዕካ ነገሥት የባዕታ ለማርያም ገዳም በመመለስ በመኪና ቀድመው መስቀል አደባባይ በመገኘት የክብር ቦታ ይዘው የበዓሉ ተካፋይ ይሆናሉ።

7. ንጉሣዊ ቤተሰቦችና ፍላጎት ያላቸው የውጭ እንግዶች የግርማዊነታቸው አጽም በነበረበት ቦታ ለታሪክ የሚቀመጠውን መታሰቢያ በባዕታ ገዳም ያኖራሉ።

8. የግርማዊት እቴጌ አስከሬን አሁን ካለበት ቦታ ወጥቶ ወደተዘጋጀለት ከግርማዊነታቸው ጎን ባለው መካነ መቃብር ይዛወራል።

9. ንጉሣዊ ቤተሰቦችና የክብር እንግዶች ወደፊት የሚሠራውን የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ጽሕፈት ቤትንና የቤተመጻሕፍት ወመዘክር የመሠረት ድንጋይ የማኖር ሥነስርዓት ላይ ይካፈላሉ።

10. አስከሬኑ ከዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ኀዳና አናት ጀምሮ የአገር ልብስ በለበሱ በላዩም ላይ የዓንበሣ ዓርማ ያለበት ሰንደቅ ዓላማ ያጌጠ ኮርዶን እና በግራ ክንዳቸው የሃዘን ጥቁር ጨርቅ ያሰሩ ሁለት መቶ ከሕብረተሰቡ የተውጣጡ አጃቢዎች በግራና ቀኝ ታጅቦ በብሔራዊ ቤተመንግሥት ፊትለፊት አልፎ በመስቀል አደባባይ የመጀመሪያ ዕረፍት ይደረጋል። የሃዘን ሙዚቃ በማሰማት ከአስከሬኑ ፊትለፊት የሚሄዱ ሙዚቀኞች ከዳግምዊ ዐፄ ምኒልክ ኀዳና አናት ጀምሮ ይመደባሉ።

ወደፊት በሚወሰነው መሠረት ጥቂት ንጉሣዊ ቤተሰቦችና ጋዜጠኞች በመኪና አስከሬኑን ይከተላሉ።

11. በመስቀል አደባባይ ለሚሰበሰበው ሕዝብ ከንጉሣዊ ቤተሰብ አንዱ እና የመታሰቢያ ድርጅቱ ሰብሳቢ እንዲሁም የክብር እንግዶችና ሕዝባዊ ወኪሎች አጭጭር የሃዘን መግለጫ ንግግር ያደርጋሉ። በዚህ አደባባይ የቆይታ ጊዜ ከአንድ ሰዓት እንዳይበልጥ ጥረት ይደረጋል። የአጃቢዎችና የሙዚቀኞች ለውጥ ከዚሁ ይደረጋል።

12. ከመስቀል አደባባይ በመነሳት ለገሃር ሲደርስ ዞረው ወደሰሜን አቅጣጫውን በመለወጥ በቸርችል ጎዳና አድርጎ ደጎል አደባባይን በመዞር ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ይገባል። በዚህ ግርማዊነታቸው ሥርዓተ ንግሥ ባደረጉበት ቤተክርስቲያን አሥራ አምስት ደቂቃ የማይበልጥ የጸሎትና ሌላም ሥነስርዕት ይፈጸማል። በዚህም የአጃቢዎችና የሙዚቀኞች ለውጥ ይደረጋል።

13. ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በመነሳት በቄዘሮል መንገድ አድርጎ አፍንጮ በርን አልፎ የየካቲት 12 አደባባይን ዞሮ በዩኒቨርሲቲው ዋና በር በማለፍ ከግርማዊነታቸው ጋር አብሮ የተሰደደው የመድኃኔዓለም ጽላት በሚገኝበት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን የሶስተኛው ዕረፍት ይደረጋል።

በዚህ ቦታ አስከሬኑ ከክብር ማጓጓዣው ተሽከርካሪ ወደሠረገላ ይዛወራል። ግርማዊት እቴጌ መነን በአረፉበት ወቅት አስከሬኑ የተጓዘበት ሠረገላ ካልተገኘ ሌላ ተመሳሳይ ማሠራት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የአጃቢዎችና የሙዚቀኞች ለውጥ በዚሁ ይደረጋል።

ከምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ጀምሮ የጀግኖች ማኅበር አባላት ማኅበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ለበዓሉ ድምቀት የሚሰጥ የክብር ልብስ በመልበስ በአጀቡ ተካፋይ ይሆናሉ። ፈረሰኛ አጃቢዎችም ከዚህ ጀምሮ ይመደባሉ። በፈረሶቹም ሆነ በፈረሰኞቹ አለባበስ የዓንበሣ ዓርማ ያለበት ሰንድቅ ዓላማ ጉልህ ቦታ እንዲይዝ ይደረጋል።

14. ከምስካየ ኅዙናን ቤተክርስቲያን በመነሳት በየካቲት 12 እና በሚያዝያ 27 አደባባዮች በማለፍ በዋናው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መግቢያ አድርጎ ለሥነስርዕቱ ወደተዘጋጀለት ቦታ አስከሬኑ በሚያመራበት ጊዜ በንጉሣዊ ቤተሰቦች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገሮች የክብር እንግዶች፣ በአጃቢነት የተሠማሩት የሕብረተሰቡ ወኪሎች፣ በጠቅላላው እስከ 10,000 (አሥር ሺህ) የሚጠጉ የሥነስርዓቱ ተካፋዮች ለአስከሬኑ አቀባበል ያደርጉለታል። ወደፊት በዝርዝር የሚዘጋጀው በካቴድራሉ ቅጥር ግቢ የሚደረገው ሥነስርዕትም እንደተፈጸመ የግርማዊነታቸው አጽም በተገቢው የክብር ቦታ እንዲያርፍ ይደረጋል።

15. አስከሬኑ በሚጓዝባቸው ጎዳናዎች ሁሉ በተለይ የተከለከሉ ቦታዎች ካልሆኑ በስተቀር ሕዝቡ ግራና ቀኙን በመያዝ ቆሞ የግርማዊነታቸውን አስከሬን ለመጨረሻ ጊዜ ይሰናበታል። የዚህም ሕዝብ ብዛት ከ400,000 እስከ 700,000 እንደሚደርስ ይገመታል፡ የዚህ የረጅም 12 ኪሎሜትር ጉዞ የተመረጠውም ሕዝቡን ያለብዙ መጨናነቅ ለማስተናገድ ታስቦ ነው። ይኸ በመንገድ የተሰለፈው ሕዝብ በጁ ይዞ የግርማዊነታቸው አስከሬን ሲያልፍ የሚያውለበልበው የግርማዊነታቸው ዓርማ ያለበት 200,000 ሰንደቅ ዓላማዎች ይታደላሉ። የታደሉት ሰንደቅ ዓላማዎቹ ሁሉ ሃዘንን እንዲያንጸባርቁ ዝቅ ብለው እንደተሰቀሉ ሆነው እንዲታዩ ይደረጋል።

16.. የቀብር ሥነስርዕቱ ከተፈጸመ በኋላ ለተከበሩ እንግዶች የሚደረገው ግብዣና ሌሎችም የጉብኝትና ተመሳሳይ ዝግጅቶች ወደፊት ይወሰናሉ።

17. ጠቅላላ ሥነስርዕቱ ዘጠኝ ሰዓት ያህል እንደሚፈጅ ተገምቷል።

18. በአማራጭ እስከ ለገሃር ያለው ጉዞ እንደተጠበቀ ሆኖ ከለገሃር ወደቸርችል ጎዳና በመታጠፍ ፊንታ በቀጥታ ሜክሲኮ አደባባይ ከደረሰ በኋላ በሚቸልኮትስና በሆቴል ደአፍሪክ መሃከል ባለው ሰፊ መንገድ ተጉዞ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን አጠገብ በሚገኘው አደባባይ ዞሮ በአንዋር መስጊድ ፊትለፊት አልፎ በፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ መንገድ በአቡነ ጴጥሮስ ሃውልትና ምኒልክ አደባባይ አድርጎ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ይገባል። በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ከላይ የተገለጸው ሥነስርዓት ከተፈጸመ በኋላ አስከሬኑ ወደሠረገላ ይዛወራል። የጀግኖች ማኅበር አባላትም አጀብ ከዚሁ ይጀምራል። ከጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ተነስቶ በራስ መኮንን ድልድይ በማድረግ በየካቲት 12 አደባባይ ዞሮ ወደቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይገባል።

19. በሌላ አማራጭ ጉዞው ከነዕታ እንደወጣ ታላቁ ቤተመንግሥትን በገብርኤል በኩል ከዞረ በኋላ ወደሰሜን በመሄድ ሚያዝያ 27 አደባባይ ሲደርስ በአድዋ (የቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ) ጎዳና በማድረግ በራስ መኮንን ድልድይ አልፎ የደጎልን አደባባይ ዞሮ በምኒልክ አደባባይ አድርጎ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ገብቶ ሲወጣ ከላይ የተዘረዘረውን መሥመር እንዲከተል በአማራጭ ተይዟል። ይኸ ጉዞውን በግማሽ ቢቀንሰውም የሚያስተናግደውም ሕዝብ በዚያው መጠን ይቀንሳል።

20. በዚሁ ዕለት በግርማዊነታቸው ሥም የሚቋቋሙት ቤተመጻሕፍት ወመዘከር ማዕከሎች ወደፊት ለዚሁ በሚዘጋጁበት ሥፍራዎች የመሠረት ድንጋዮች ማኖር ሥነስርዓት ይፈጸማል። እንዲሁም የግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ የስኮላርሽፕ ተቋም ሥራውን መጀመሩን ለሕዝብ ይገለጻል።

21 የመንበረ ጸባዖት ቅዳት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት፣ በመካነ መቃብሩ አካባቢ የወለልና የግድግዳ ዕብነበረድ ማልበስ፣ መግቢያና መውጫዎችን ማዘጋጀት፣ ወዘተ፣ አስቀድመው መጠናቀቅ አለባቸው። በግቢውም ውስጥ ለንጉሣዊ ቤተሰቦችና ለክብር እንግዶች ማረፊያና ለሥነሥርዓቱ አስፈላጊ ሥራዎችን ሁሉ በባለሞያ ተጠንተው መሠራት ይኖርባቸዋል።

22. በየክልሉቹ በዕለቱ ስለሚደረገው ሥነሥርዓት ዝርዝር ፕሮግራም ይወጣል። መታሰቢያ ድርጅቱ እንደተመዘገበ በክልሎች በየዞኑ ኮሚቴዎች ተቋቋመው የሕዝቡ ተሳትፎ እንዲኖር እርምጃ ይወስዳሉ። በአዲስ አበባ የቀብሩ ሥነስርዓት በሚፈጸምበት ዕለት በተወካይነት አዲስ አበባ ለሥነስርዕቱ ተካፋይነት የሚገኙትን አባላት ይመርጣሉ።

23. ከሥራ ኢፈጻሚው ኮሚቴ ጋር በመመካከር የግርማዊነታቸው አጽም የሚያርፍበትን ሣጥን ንጉሣዊ ቤተሰቦች ያቀርባሉ።

24. በዕለቱ ታሪካዊ ሥነስርዓቱ በቪዲዮና በመሣሉ የሚቀረሰበትን ሁኔታ የሕዝብ ግንኙነቱ ኮሚቴ ያዘጋጃል።

25. ከመንግሥት ጥበቃ ኃይል ጋር በመካከር ሥነስርዓት በሚካሄድባቸው ቦታዎችና አስከሬኑ በሚጓዝባቸው መንገዶች ሁሉ ጥበቃውና የሕዝብ ማስተናገዱ በመታሰቢያ ድርጅቱ ኃይል ጭምር በመሆኑ ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገውን የድርጅቱ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ዝርዝር ጥናት በማድረግ ዝግጅቱ አስቀድሞ እንዲጠናቀቅ የአስተናባሪ ኮሚቴ እንቅስቃሴ በአስቸኳይ እንዲጀመር ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ መመሪያ እንዲሰጥበት ይጠበቃል።

26. የሕዝብን ሙሉ ተሳትፎ ለማረጋገጥና የመንገዶችንም መጨናነቅ ለመቀነስ የቀብሩ ሥነስርዓት በሕዝብ በዓልና ከግርማዊነታቸው ጋር በተያያዘ ቀን እንዲሆን የሚመረጥ ሲሆን የግርማዊነታቸው ልደትና የዘውድ በዓል ቀናት ኦፊሲያል የሕዝብ በዓላት ባለመሆናቸው በነዚህ ቀናት የቀብሩን ሥነስርዓት ለመፈጸም አዳጋች ይሆናል። የልደት ቀናቸው በበዓል ቀን ቢውልም እንኳ የክረምት ጊዜ በመሆኑ ለበዓሉ አከባበር አመቺ አይሆንም። ስለሆነም የቀብሩ አፈጻጸም ሚያዝያ 27 ቀን ለመሆኑ አማራጭ አይኖረውም። መታሰቢያ ድርጅቱ የቀብሩ ሥነስርዓት የሚፈጸመው ሚያዝያ 27 ቀን 1991 ዓም እንዲሆን በመገንዘብ አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ በዚህ ዓላማ ተመሥርቶ እንዲጠናቀቅ ጥረት እንዲደረግ የአጽም በክብር ማዛረፍ ኮሚቴ ዝርዝሩን ሥራ እንዲቀጥልበት መመሪያ ሰጥቷል።